የኢሕአፓ 36ኛ የምሥረታ በዓል በድምቀት ተከበረ

36 ክረምትና 36 በጋ በትግል ላይ ያለው ኢሕአፓ በዋሽንግተን ዲሲ ቅዳሜ ጥቅምት 15 ቀን 2001 አክቶበር 25 ቀን 2008 ምሽቱን በኢትዮጵያዊነት ስሜት የምሥረታ በዓሉን አክብሯል።

ክረምት መግባቱን ለማብሠር የተለቀቀ ይምስል የወረደውን ዶፍ ዝናብ ከቁብ ሳይቆጥር ለኢሕአፓ ሰማዕታት ክብር ሲል ለሀገሩ ነፃነት ቀናዒነቱንም ለመግለጽ ፥ የትግል አጋርነቱን ለማሳየት፥ አዳራሹን የሞላው ታዳሚ፥ ለወደቁት ሰማዕታት ደብዛቸውን የጠፋ ጓዶችን ለመዘከር ነበር ከመቀመጫው ብድግ ብሎ አንደ እየምነቱ በዓሉን በፀሎት የጀመረው።

ከዋሽንግተን ዲሲ ፥ ከቬርጂኒያ፥ ከሜሪላንድ፥ ከኒውዮርክ፥ ከፊላደልፊያ፥ ከቦስተን ከሚቺጋን፥ ከሲያትል ፥ ከካናዳና ከአውሮፓ ዝክረ በዓሉን፥ ለመካፈል የተሰባሰበው ኢትዮጵያዊ ከመድረኩ እንግዶች ተራ በተራ በዘረዘሩት ትምህርታዊ፥ ታሪካዊና ቁርጠኛነት የተቀላቀሉበትን ንግግሮች ያለመሠልቸት ነበር በጥሞና አድምጦ በታላቅ አድናቆት የተቀበለው።

ከበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴ የቀረበውን አጭር የፅሁፍ መልክት ያቀረቡት ከፊላደልፊያ ጓድ ካሣሁን ሲሆኑ የዛሬውን በዓል ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ልዩነትን በውይይት ከመፍታት ይልቅ በጉባዔ ረገጣ ኢዴሞክራሲያዊነታቸውን ያረጋገጡ ሣልሣዊ አንጃዎች ያደረሱብንን ጉዳት ጠግነን ህልውናችንን ያረጋገጥንበት ሰዓት ላይ መድረሳችንን ነው የሚያደርገው ብለዋል። በዓሉን ልዩ የሚያደርገው ሁለተኛ ምክንያት ኢትዮጵያ ከመቸውም ዘመን በከፋ መልኩ የጣር ጩኸት እያሰማች ያለችበት የቁርጥ ትግል ሰዓት ላይ እያለን በዓሉ መከበሩ በአደባባይ ለሕዝባችን የገባነውን ቃል ኪዳን ለማደስ መድረክ በማግኘታችን ነው ብለዋል።

በዘንድሮው የ36ኛ ዓመት የኢሕአፓ ምሥረታ በዓል ላይ የፓርቲውን መልእክት ለማስተላለፍ በእንግድነት የተጋበዙት የኢሕአፓ አመራር አባል ጓድ ፋሲካ በለጠ ሲሆኑ እሳቸውም ባስተላለፉት መልእክት የዛሬውን በዓል የምናከብረው ዓመት ቆጥረን ራሳችን ለማመጻደቅ ወይም ወይም ሻማ አብርተን ለመደሰት ሳይሆን የኢትዮጵያ ጠላት የሆነውን የወያኔን አገዛዝ በሁለ ገብ ትግል ለማስወገድ ቃል ኪዳናችንን ለማድስና የወደቁ ጓዶቻችን ለመዘከር ነው የሚሉ ቃሎችን ሲያስሙ የስምምነትና የድጋፍ ጭብጨባ ከቤቱ ተስተጋብቷል።

የኢሕአፓን የቀን ተቀን እንቅስቃሴ በቅርብ ርቀት የምከታተል ወዳጅ ነኝ ያሉት ዕውቁ ኢትዮጵያዊ ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ ሲሆኑ በዕለቱ ለኢሕአፓ የሰጡት ከእምነት የሠረፀ ምስክርነት የቤቱን ቀልብ በጣሙኑ የሳበ ንግግር እንደነበር ነው ሁሉም የተስማማበት። ፕሮፌሰር መስፍን ሲናገሩ ኢሕአፓ ላለፉት 18 ዓመታት ለኢትዮጵያ ሲል ያደረገውን የኅብረት ጥረትና ድካም እያደነቁ ከዚህ በኋላ ግን ድርጅቱ ራሱን በማጠናከር ላይ አተኩሮ ከተንቀሳቀሰ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል ድምዳሜ ላይ መድረሳቸውን የሚገለጽ አስተያየት ሲሰጡ በአዳራሹ ውስጥ የነበረው አድማጭ ድጋፉን በጋለ ጭብጨባና ሞራል ነበር የተቀበለው።

ሌላው የበዓሉን ደማቅነት ካጎላው አንዱ ድንቅ ሥራ የሠሩ ኢትዮጵያውያንን ማስተዋቁና ክብርና የመስጠት መርሃ ግብር ነበር። ቀዳሚውን ሰዓት የወሰዱት አባት አርበኛ 4 መንግሥታትን ማለትም ወራሪውን ጣሊያን ጨምሮ የአፄውን የደርግንና አሁንም የወያኔ ሥርዓቶችን በፅኑና አምርረው በመታገል የታወቁት የ95 አመቱ የዕድሜ ባለፀጋ ኮ/ል አስናቀ እንግዳ ነበሩ። የኢሕአፓ ጠበቃ አባት አስናቀ በድካም ምክንያት መምጣት ባይችሉም የእንኳን አደረሳችሁ መልእክታቸው ተላልፎ ፓርቲውም አባላቱም ለአርበኛው አስናቀ እንግዳ ረዥም ዕድሜ ከጤና ጋር ፈጣሪ ሰጥቷቸው ለሀገራችው ነፃነት እንዲበቁ ምኞቱን አስተላልፏል።

በበዓሉ ምክንያት ምስጋናና አድናቆት የቀረበላቸው ሌላዋ የ75 ዓመቷ የዕድሜ ባለፀጋ ደግሞ እናት (ማዘር) አሰለፈች ነበሩ። ገድላቸው ከተዋወቀ በኋላ ጠቅላላ ከበዓሉ ዕድመተኞች ማቋረጫ ያጣ የሞቀ ጭብጨባ በታላቅ ስሜት ተበርክቶላቸዋል።

በመርሃ ግብሩ መሠረት ኢሕአፓ ወራሽ ያለው ቀጣይ ፓርቲ መሆኑን በሚገባ ያስረገጠ በሳልና ይበል ይበል የሚያሰኝ ጽሁፍ በወጣት ውብሸት ቀርቧል። የዚህ የወጣት ክንፍ አባል የሆነው ወጣት ሙሉ ንግግር በድረ ገጽ ወይም በፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ የሚሰማ ሲሆን ውብ አቀራረብና ድንቅ የሀገር ፍቅር ስሜት ያዘለው ጽሁፍ ከፍተኛ  አድናቆትን ከማግኘቱ ሌላ ወላድ በድባብ ትሂድ አሰኝቷል።

በበዓየኢትዮጵያ መድሕን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፥ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅትና የኦሮሞ ነፃነት ድርጅት ( ኢብሶ) ተወካዮች በበዓሉ ላይ ተገኝተው የትግል አጋርነታቸውን የገለጹ ሲሆን የመድኅን ተወካይ ልጅ ሠይፉ ዘውዴ በትግል አጋርነታቸው ለፓቲው ያላቸውን ድጋፍና እንዲሁም ሁሉም ለኅብረት ትግሉ አጽንኦት ሰጥቶ ትግሉን ማጠናከር እንዳለበት ጥሪ የሚያደርግ ንግግር አሰምተዋል። ከሚደያ ድርጅቶች የአሲምባ የውይይት መድረክ፥ የነፃነት ለኢትዮጵያ ራዲዮ፥ የኢትዮጵያዊነት ራዲዮ፥ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዩ ተወካዮች ተገኝተው ለበዓሉ ድምቀት አስተዋጽኦ ያደረጉ ከመሆኑም በላይ የአሲምባ የውይይት መድረክ ተወካይ አቶ ኤሊያስ ጠንክር የድጋፍ መልእክት አስተላልፈዋል።  ከኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ የድጋፍ መልእክት የተሰማ ከመሆኑም በላይ በአውሮፓ የኢሕአፓ ኮሚቴ አባል ጓድ አቢይ ሳህሉ ስሜት የሚኮረኩር የድጋፍ መልእክት አሰምተዋል።

በመጨረሻም የሚችጋኑ ነዋሪ ጓድ ጌታሁን “ በእግር መሄድ ሳለ” በሚል ውስጠ ወይራ ግጥም አሰምተዋል። ጓድ አሊ ሁሴንም እንዲሁ የማይሰለችውና ለበዓሉ ተስማሚ የሆነውን ግጥማቸውን አሰምተዋል። በጓድ አሊ ሁሴን የተቀነባበረ የኢሕአፓን ታሪክ የሚገልጽ ዶክመንተሪ ፊልም ለናሙና ያህል ከታየ በኋላ ለዘመናት በሚለው መዝሙር በዓሉ ተጠናቋል። በዓሉ እንዲሳካ በማድረግ ላደረገችው ጥረት ከፍተኛ ምስጋና የተለገሳት አርቲስት ጠለላ ከበደና ለበዓሉ ክብር በበጎ ፈቃደኛነት የተሳተፉ አርቲስት ማሪቱ ለገሠና አርቲስ ሰጠኝ አጠና በባህላዊ ሙዚቃ ዕድምተኛውን እስከእኩለ ሌሊት አዝናንተውታል።